MCPS MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
www.montgomeryschoolsmd.org MARYLAND

Malcolm Baldrige National Quality Award
2010 Award Recipient

ሴፕተምበር, 2017

የተከበራችሁ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች፡-

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) እያንዳንዱ ተማሪ ለኮሌጅ፣ ለስራ፣ እና ለህይወት/ለኑሮው በሚገባ ዝግጁ ሆኖ ከት/ቤቶቻችን መመረቁን ለማረጋገጥ ግዴታ ገብቷል። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጉዞ ለመማርና ለመመራመር እናም ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ በአስገራሚ እድሎች የተሞላ የሚያስደስትና የሚያጓጓ ጉዞ ነው። በነዚህ አራት አመታት ውስጥ፣ መምህራኖቻችንና ሰራተኞቻችን ለተማሪዎቻችን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት እና በሜሪላንድ ስቴት ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁ እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ጥብቅ ተፈላጊዎችን የሚያሟላ ከፍተኛ-ብዓለም ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት ይተጋሉ። ከነዚህ ተፈላጊዎች ጥቂቶቹ ከቅርብ አመታት ወዲህ ተለውጠዋል፤ ስለሆነም ተማሪዎቻችን በወቅቱ መመረቃቸውንና ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ጥናቶች/ትምህርት መስመር ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቤተሰቦች ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤታቸው አማካሪ ጋር መተባበር ወሳኝና አስፈላጊም ነው።

የኮርስ ክሬዲቶች፣ የስቴት ፈተና፣ እና ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነትን በሚመለከት ሁሉም ቤተሰቦች ግንዘቤ እንዲኖራቸው ተፈላጊዎቹን በጥራት ለመዘርዘር MCPS ይህን መገልገያ ያቀርባል። የ የ*2013* የኮሌጅና የስራ ዝግጁነት እና የኮሌጅ አፈፃፀም ተግባር/ደንብ *"College and Career Readiness and College Completion Act of 2013"*{5}፣ **በሜሪላንድ ጠቅላላ ምክር ቤት የተላለፈው፣ ሁሉም ተማሪዎች 11ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ በእንግሊዘኛና በሂሳብ ከበርካታ ግምገምዎች በአንዱ እንዲገመገሙ ይጠይቃል።** የተወሰነ ውጤት/ማርክ የማያገኙ ተማሪዎች 12ኛ ክፍል ውስጥ የመሸጋገርያ ኮርስ መውሰድና አንድ ግምገማ እንደገና መውሰድ ይገባቸዋል። ለክትትል እንዲጠቅምዎ ስለ ግምገማዎቹ እና የማለፊያ ማርኮች ተጨማሪ ዝርዝሮች እዚህ ተካትተዋል። በተጨማሪም፣ በየትኛው ዓመት ተማሪው/ዋ 9ኛ ክፍል እንደገባ/ች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ መውሰድ ያለባቸው ተፈላጊዎች እና በስቴት የሚወሰነው የቴስት/ፈተና ማለፊያ ውጤቶች ይለያያሉ። ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ስለ ልዩ ሁኔታቸው ጥያቄዎች ካሏቸው እገዛ/እርዳታ ለማግኘት ከአማካሪዎቻቸው ጋር መመካከር ይችላሉ።

ከት/ቤቶቻችን በያንዳንዳቸው በሚጠብቋቸው የሚያጓጉና አስገራሚ እድሎች በተቻላቸው መጠን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተማሪዎቻችንን አደፋፍራለሁ። በያንዳንዱ ት/ቤት የሚገኙ መምህራን፣ አማካሪዎች፣ እና አስተዳዳሪዎች ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ እና ከምረቃ በኋላ ህይወት የሚያቀርባቸውን እድሎች ለመጨበጥ በሚገባ መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ በተጠንቀቅ ቆመዋል።

ከአክብሮት ጋር፣

Jack R. Smith, Ph.D.
ዶ/ር ጃክ ር. ስሚዝ
Superintendent of Schools
የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

# ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 5 ዓመት

የመጀመርያ አመት ዘጠነኛ ክፍል፡- 2013–2014

# የMCPS ምረቃ ተፈላጊ መስፈርቶች በጨረፍታ

የሜሪላንድ ስቴት አንድ ዲፕሎማ ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተመራቂዎች ይፈቅዳል፣ በአራት መሟላት የሚገባቸው ፈርጆች ስኬታማ ክንውን ላይ በመመስረት፡- ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት፣ የተማሪ ትምህርታዊ አገልግሎት፣ (SSL)፣ እና የሜሪላንድ ምዘና-ግምገማዎች። ሌሎች ሁሉም ተፈላጊዎች ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ተገልፀዋል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ የMCPS High School Course Bulletin/የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ መፅሄት በhttp://coursebulletin.montgomeryschoolsmd.org ወይም የት/ቤትዎን አማካሪ አማክሩ።

<table>
<tr><th colspan="4">የኮርስ ክሬዲቶች</th></tr>
<tr><td>እንግሊዘኛ</td><td colspan="3">4 ክሬዲቶች</td></tr>
<tr><td>ኪነ-ጥበባት</td><td colspan="3">1 ክሬዲት በኪነት፣ ጭፈራ፣ ትያትር፣ እና በሙዚቃ ምርጥ ኮርስ ይህን ተፈላጊ ያሟላል።</td></tr>
<tr><td>የጤና ትምህርት</td><td colspan="3">0.5 ክሬዲት</td></tr>
<tr><td>የሂሳብ ትምህርት</td><td colspan="3">4 ክሬዲቶች 1 ሙሉ-አመት (A/B) የአልጀብራ ክሬዲት እና 1 የጂዮሜትሪ ክሬዲት ያስፈልጋሉ። አንድ የካልኩለስ ኮርስ በስኬታማነት የፈፀሙ ተማሪዎች ከዚህ የ4-ክሬዲት ተፈላጊ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ።</td></tr>
<tr><td>የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት</td><td colspan="3">1 ክሬዲት</td></tr>
<tr><td>ሳይንስ</td><td colspan="3">3 ክሬዲቶች 1የባዮሎጂ ክሬዲት እና 1 የፊዚካል ሳይንስ ክሬዲት መካተት አለባቸው።</td></tr>
<tr><td>የህብረተሰብ ሳይንስ</td><td colspan="3">3 ክሬዲቶች 1 የዩ.ኤስ. ታሪክ ክሬዲት፣ 1 የአለም ታሪክ ክሬዲት፣ እና 1 ብሄራዊ፣ የስቴት፣ እና ያካባቢ አስተዳደር ክሬዲት ይፈለጋሉ።</td></tr>
<tr><td>የቴክኖሎጂ ትምህርት</td><td colspan="3">1 ክሬዲት ይህንን ለማሟላት ተፈላጊ የሆኑ ኮርሶች በኮርስ መፅሄት ላይ ተገልጸዋል</td></tr>
<tr><td rowspan="2">በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶች ለምረቃ የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ክሬዲቶች ከሚቀጥሉት ሶስት አማራጮች በአንዱ መሟላት ይቻላል፡-</td><td>ምርጫ 1</td><td>ምርጫ 2</td><td>ምርጫ 3</td></tr>
<tr><td>2 ክሬዲቶች በአለም ቋንቋ ወይም<br>2 ክሬዲቶች በአሜሪካዊ የምልክት ቋንቋ<br>እና<br>2.5 ክሬዲቶች ተመርጠው በሚወሰዱ (elective) ኮርሶች</td><td>2 ክሬዲቶች በላቀ የቴክኖሎጂ ትምህርት<br>እና<br>2.5 ክሬዲቶች ተመርጠው በሚወሰዱ (elective) ኮርሶች</td><td>4 ክሬዲቶች ስቴት ባፀደቀው የጥናት ፕሮግራም<br>እና<br>0.5 ክሬዲት ተመርጠው በሚወሰዱ ኮርሶች</td></tr>
<tr><th colspan="4">STUDENT SERVICE LEARNING/የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)</th></tr>
<tr><td>የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL)</td><td colspan="3">75 የአገልግሎት ትምህርት ሰዓቶች</td></tr>
<tr><th colspan="4">የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ግምገማ (MHSA) ተፈላጊዎች<br>የHSA፣ PARCC፣ እና የMISA ግምገማዎች<br>የMHSA ተፈላጊዎች በሜሪላንድ የትምህርት መምሪያ (MSDE) ሊለወጡ ይችላሉ።</th></tr>
<tr><td>አልጀብራ 1</td><td colspan="3">በአልጀብራ 1 የተገኝ ይeኮርስ ክሬዲት፣ እና<ul><li>የአልጀብራ 1 PARCC ወይም የአልጀብራ 1 HSA ከ2016–2017 በፊት መውሰድ፣ ወይም</li><li>የአልጀብራ 1 PARCC በ2016–2017 ወይም በ2017–2018 መውሰድ እና በጁን 2018 መመረቅ፣ ወይም</li><li>አልጀብራ 1 በPARCC ማለፍ</li></ul></td></tr>
<tr><td>ባዮሎጂ/Maryland Integrated Science Assessment/የሜሪላንድ የተወሀሀደ የሳይንስ ግምገማ (MISA)</td><td colspan="3">በባዮሎጂ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት፣ እና<ul><li>ባዮሌጂ HSA ከ2016–2017 በፊት ማለፍ፣ ወይም</li><li>ባዮሌጂ HSA በ2016–2017 ውስጥ መውሰድ፣ ወይም</li><li>በ2017–2018 ወይም በ2018–2019 ውስጥ የMISA ስህተት-የለሽ የመስክ ፈተና መውሰድ</li></ul></td></tr>
<tr><td>እንግሊዘኛ 10</td><td colspan="3">በእንግሊዘኛ 10 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት ወይም ESOL 3 ወይም ከዚያ በላይ፣ እና<ul><li>የእንግሊዘኛ ቋንቋ ኪነጥበባት/መሰረተትምህርት(ELA/L) 10 PARCC ወይም እንግሊዘኛ 10 HSA ከ2016–2017 በፊት መውሰድ፣ ወይም</li><li>ELA/L 10 PARCC በ2016–2017 ወይም በ2017–2018 ውስጥ መውሰድ እና በ ጁን 2018 መመረቅ፣ ወይም</li><li>ELA/L 10 PARCC ማለፍ</li></ul></td></tr>
<tr><td>የመንግስት አስተዳደር</td><td colspan="3">በአገር፣ ስቴት፣ እና በአካባቢ አስተዳደር የተገኘ የኮርስ ክሬዲት፣ እና<ul><li>የመንግስት አስተዳደር በHSA ማለፍ</li></ul></td></tr>
</table>

[1] Substitute Test/ተተኪ ፈተና—በተተኪ ፈተናዎች (AP/IB) አጥጋቢ ውጤቶች የሚያገኙ ተማሪዎች የMHSA ተፈላጊ በዚያ ይዘት መስክ ያሟሉታል።

[2] በዝውውር ምክንያት የሚያዝላቸው ክሬዲት፡—ከሜሪላንድ የህዝብ ት/ቤቶች ውጭ ተዛውረው የሚመጡ ተማሪዎች በዝውውር ሲመጡ የተወሰኑ ክሬዲቶች የMHSA ደረጃ/መመዘኛ ለማሟላት ብቃት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል።

[3] የተጣመሩ/የተያያዙ የፈተና ውጤት አማራጮች ለHSAዎችና ለPARCC ግምገማዎች ይገኛሉ።

[4] የመሸጋገርያ እቅድ "Bridge Plan"—ማለት የMHSA ለምረቃ ተፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት ሌላኛው አማራጭ ነው። በመሸጋገርያ እቅድ አማካይነት፣ መደበኛውን ፈተና ማለፍ የሚያዳግታቸው ተማሪዎች ፕሮጀክቶችን በማከናወን የመረዳት/የማወቅ ችሎታቸውን ያረጋግጣሉ/ያሳያሉ።

# ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት

በ2013 የሜሪላንድ ጠቅላላ ጉባኤ ለኮሌጅና ለሥራ ዝግጁነት፡ እና ኮሌጅ ስለማጠናቀቅ፡ ሁሉም ተማሪዎች በኮሌጅ ውስጥ ክሬዲት በሚያስገኝላቸው ኮርስ ስራ እና ተመጣጣኝ ክፍያ የሚያስገኙ ስራዎች ላይ ያተኮረ የ (CCRCCA) ደንብ/መመሪያ አሳልፏል። ደንቡ በተጨማሪ 11ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ላይ ሁሉም ተማሪዎች ከብዙ ወደ ኮሌጅ እና ሥራ መግቢያ ምዘና ዘይቤዎች አንዱን በመጠቀም የእንግሊዝኛ እና የሂሳብ ፈተና እንደሚወስዱ ይደነግጋል። 11ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት መመዘኛ በእንግሊዝኛ ወይም በሂሳብ ያላሟሉ ተማሪዎች 12ኛ ክፍል ውስጥ ለዳግመ-ግምገማ ዝግጅት በመሸጋገርያ ኮርስ ወይም በሌላ የትምህርት እድል መመዝገብ ይኖርባቸዋል። የመሸጋገርያ ኮርስ ወይም የትምህርት እድል ከፈፀሙ በኋላ፣ ተማሪዎች 12ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ እንደገና መፈተን/መገምገም አለባቸው። የት/ቤት አማካሪዎችና ሰራተኞች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ከሁሉም የበለጠውን ግምገማ ለመውሰድ፣እንዲሁም 12ኛ ክፍል ላይ ካስፈለገ፣ የሽግግር ኮርስ አማራጮችና ዳግም-ግምገማ ለመወሰን ከተማሪዎች ጋር በቅርብ ሆነው ይሰራሉ።

## በMCPS ውስጥ ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁነትን የሚወስኑ መመዘኛዎች ምንድን ናቸው?

| ከሚከተሉት ግምገማዎች አንዱ ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት በሒሳዊ ምንባብ/እንግሊዝኛ የቋንቋ ኪነጥበብ ሊወስን ይችላል። | |
|---|---|
| **SAT**፡- | 500* ወይም የበለጠ |
| **ACT**፡- | 21 ወይም ከዚያ በላይ |
| ልዩ ፈተና/**ACCUPLACER**፡- | ምንባብ 79 ወይም ከዚያ በላይ<br>የአረፍተነገር ክሂሎቶች 79 ወይም ከዚያ በላይ |
| የላቀ ደረጃ ቋንቋ እና ድርሰት አጻጻፍ ወይም የላቀ ደረጃ ቋንቋ እና ስነጽሑፍ፡- **(Advanced Placement (AP) Language and Composition or AP Language and Literature)** | 3 ወይም ከዚያ በላይ |
| **(IB)** እንግሊዝኛ **(International Baccalaureate)**፡- | 4 ወይም ከዚያ በላይ |

| ከሚከተሉት ግምገማዎች አንዱ ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት በሂሳብ ትምህርት ሊወስን ይችላል፡፡ | |
|---|---|
| **SAT**፡- | 500* ወይም የበለጠ |
| **ACT**፡- | 21 ወይም ከዚያ በላይ |
| ልዩ ፈተና/**ACCUPLACER**፡- | ኤሌሜንታሪ አልጄብራ 62 ወይም ከዚያ በላይ<br>የኮሌጅ ደረጃ ሂሳብ 45 ወይ ከዚያ በላይ |
| የላቀ ምደባ **(AP)** ካልኩለስ AB ወይም **BC**፣ወይም **AP** ስታትስቲክስ፡- | 3 ወይም ከዚያ በላይ |
| **(International Baccalaureate) (IB)** ሒሳብ፡- | 4 ወይም ከዚያ በላይ |

* ሞንጎመሪ ኮሌጅ ክለሳ በተደረገው "SAT" መሠረት ለኮሌጅ ዝግጁነት መመዘኛ እስከሚጸድቅ ድረስ በጊዜያዊነት የሚጠቀምበት ውጤቶች።

**ወይም**

የስራና የቴክኖሎጂ ትምህርት ወደ ሙያዊ የስራ ፈቃድ ወይም ኢንዱስትሪ ሠርተፊኬት የሚያመራ ውጫዊ ግምገማ "Career and Technology Education"(CTE) ይመልከቱ፡-www.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/info/CCRCCA/certifications-041217.pdf የልዩ ፕሮግራሞችን ዝርዝር ለማግኘት

**ወይም ከሞንጎመሪ ኮሌጅ ጋር የተደረገ የአካባቢ ስምምነት፡-**

በሞንጎመሪ ኮሌጅ (Montgomery College) ከውጭ ከፍተኛ ግምት/ዋጋ የተሰጠው አጠቃላይ የፅሁፍ ግምገማ

ወይም

B ወይም ከዚያ የሚበልጥ ውጤት በዘመናዊ የዓለም ታሪክ (ማንኛውም ደረጃ)፣ AP ቋንቋ እና ድርሰት፣ ወይም የላቀ ደረጃ እንግሊዝኛ 12

በሞንጎመሪ ኮሌጅ (Montgomery College) በውጭ ፈታኝ የተረጋገጠ የማጠቃለያ የሂሳብ ግምገማ

ወይም

B ወይም ከዚያ በላይ በአልጄብራ II (ማንኛውም ደረጃ)

## ተማሪው/ዋ በ11ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ተፈላጊውን ካላሟላ(ች)ስ?

11ኛ ክፍል መጨረረሻ ላይ መመዘኛ ያላሟሉ ተማሪዎች የCCRCCA አካል በመሆን 12ኛ ክፍል ውስጥ በመሸጋገርያ ኮርስ ወይም በሌላ የትምህርት እድል መመዝገብ አለባቸው። የመሸጋገርያ እድል ከፈፀሙ በኋላ፣ 12ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ዳግመ-ግምገማ መፈተን አለባቸው። መሸጋገሪያ/ማሟያው አማራጭ የሚያካትተው፡-

1. ለዳግመ-ምዘና (ፈተና) ዝግጅት የትምህርት ሞዱዩሎችን ኢንተርኔት ላይ መከታተል/መፈጸም።
2. በተማሪው/ዋ ፕሮግራም ውስጥ የኮሌጅ ፈተና ዝግጅት/Prep፣ AP ወይም IB እንግሊዝኛ እና/ወይም የሂሳብ ኮርሶች፣ወደ በMSDE-የፀደቀ/ተቀባይነት ያለው የስራና የቴክኖሎጂ ትምህርት (CTE) ወደ ኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀት የሚያመራ ፕሮግራም፣ ወይም ከMontgomery College ጋር በመተባበር የሚቀርብ የመሸጋገርያ ኮርስ በመሰለ ኮርስ መመዝገብ።
3. ለዳግመኛ-ግምገማ/ፈተና ዝግጅት የሚያበቃ ተጨማሪ ጊዜና ይዘት የሚሰጡ ማሻሻያዎች ጋር በሚቀጥለው የእንግሊዝኛ ወይም የሂሳብ ኮርስ መመዝገብ።

## ተማሪዎች የትኛውን ፈተና እንደሚወስዱ እና የመሸጋገርያ የኮርስ ስራ ያስፈልግ እንደሆነ እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ?

በ11ኛ ክፍል ከሁሉም የበለጠውን ግምገማ ፣ እንዲሁም በ12ኛ ክፍል ካስፈለገ፣ ዳግመኛ-ፈተና/ምዘና አማራጮችን ለመወሰን የት/ቤት አማካሪዎችና ሰራተኞች ከተማሪዎች ጋር በቅርብ ተገናኝተው ይሰራሉ።

## ስለ ፈተና አማራጮች፣ የልጄ የትምህርት ይዘት፣ እና ስለ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የልጅዎን ት/ቤት አማካሪ ወይም የኮሌጅና ስራ መረጃ አስተባባሪ ያነጋግሩ። ተጨማሪ መረጃ በድረ-ገጽ www.montgomeryschoolsmd.org ሊገኝ ይችላል፡- “CCRCCA”ን ይመልከቱ።

0159.18 • EGPS • WEB • Amharic

Para leer este documento en español, ingrese a www.montgomeryschoolsmd.org/info/ccrcca/

Pour lire ce document en français veuillez consulter le site web: www.montgomeryschoolsmd.org/info/ccrcca/

請訪問網站www.montgomeryschoolsmd.org/info/ccrcca，查閱這份文件的中文譯本

Để đọc tài liệu này bằng tiếng Việt www.montgomeryschoolsmd.org/info/ccrcca/

한국어 번역판을 봅시다. www.montgomeryschooldmd.org/info/ccrcca/

**ይህን በአማርኛ ለማንበብ** www.montgomeryschoolsmd.org/info/ccrcca/**ን ይጎብኙ**